የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፰
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.58
ADDIS ABABA 4th July, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፯/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትን ህጋዊ ሰውነት ለመስጠት የወጣ አዋጅ…ገጽ ፲፪ሺ፮፻፲፫

## Content

Proclamation No.1207/2020

A proclamation to provide Legal personality to Ethiopian Islamic Affairs General Council ……………………….……….................Page 12,613

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፯/፪ሺ፲፪

### የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትን ህጋዊ ሰውነት ለመስጠት የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ፳፯(፪) በዜጎች የሃይማኖት አስተዳደር ተቋማት የማቋቋም መብት በመጠቀም ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ያቋቋሙትን ሀገር አቀፍ ተቋም የህግ ሰውነት በህግ መስጠት በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት በተግባር ደረጃ እውቅና ያለው የህዝብ ተቋም እንደመሆኑና ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ያለውን የሙስሊም ማህበረሰብ በመንግስት ዘንድና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚወክል በመሆኑ ህጋዊ ሰውነትና እውቅና በአዋጅ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ ፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION No.1207/2020

### A PROCLAMATION TO PROVIDE LEGAL PERSONALITY FOR ETHIOPIAN ISLAMIC AFFAIRS GENERAL COUNCIL

WHEREAS, it has become necessary to provide legal personality on the national institution organized by Ethiopian Muslims in accordance with the right to establish citizens' rights to religious administration institutions based on Article 27(2) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

WHEREAS, it has become necessary to provide legal personality to Ethiopian Islamic Affairs General Council which is a public institution that has a defacto recognition and that represents a large number of Muslim community in relation to the government as well as internationally.

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትን ህጋዊ ሰውነት ለመስጠት የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፯/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. ህጋዊ ሰውነት**

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትና በስሩ የተቋቋሙና የሚቋቋሙ የሃይማኖት ተቋማት ድርጅቶችና ማህበራት የተለየ ምዝገባ ሳያስፈልጋቸው በዚህ አዋጅ መሰረት የህግ ሰውነት ተሰጥቷቸዋል፡፡

**፫. ስያሜ**

ተቋሙ በሙሉ ስሙ "የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት" ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ለአርማ ፣ ለማህተምና ለቲተሮች አጠቃቀም አመቺነት እንደአስፈላጊነቱ በአጭር ስም ሊጠራ ይችላል፡፡

**፬. ስለበጀት**

፩/ የምክር ቤቱ በጀት ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር በሚገኙ ስጦታዎች፣ ከሙስሊሙ ማህበረሰብ በሚሰበሰቡ መዋጮዎች፣በሃይማኖቱ ከተፈቀዱ የአገልግሎት ክፍያዎችና እርዳታዎች የሚሸፈን ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች በሀገሪቱ ተፈፃሚነት ያላቸውን የታክስና የንግድ አሰተዳደር ህጎች መሠረት አድርጎ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ እና የልማት ሥራዎችን ይሰራል

፫/ ምክር ቤቱ ግልፅ የፋይናንስና የገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት ይኖረዋል፡፡

**፭. የስራ ቋንቋ**

የምክር ቤቱ የስራ ቋንቋ የፌደራልና የየክልሉ የሥራ ቋንቋዎችን መሰረት አድርጎ በመተዳደሪያ ደንቡ ይወሰናል፡፡

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "A proclamation to provide Legal personality to Ethiopian Islamic Affairs General Council No. 1207/2020".

**2. Legal Personality**

In accordance with this Proclamation Ethiopian Islamic Affairs General Council and religious institutions, organizations and societies established and to be established under it shall have legal personality without requirements of especial registration.

**3. Heading**

The institution may be cited with its full name "Ethiopian Islamic Affairs General Council" and may also be referred to using an abbreviation for convenience of usage in emblems or official seal or stamps as may be necessary.

**4. Budget**

1/ The budget of the Council shall be covered by gifts obtained from in and out of the country, Contributions collected from Muslim communities, service fees and donations allowed by the religion.

2/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (1) of this Article the Council can engage in additional income generating and development activities pursuant to other tax and commercial administration laws of the country.

3/ The Council shall establish a clear and transparent Financial Administration system.

**5. Working Language**

The working language of the Council shall be determined by bylaws taking in to account the Federal and Regional working languages.

**፮. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

፩/ ከዚህ አዋጅ በፊት በሁሉም የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት (መጅሊስ) ተብለው በሚጠሩ የምክር ቤቱ አካላት ያፈሯቸው ንብረቶች፡ መብትና ግዴታዎቻቸው በሙሉ እንደተጠበቁ ይቆያሉ፡፡

፪/ ጠቅላይ ምክር ቤቱ የውስጥ አሰራሩን እና አደረጃጀቱን ለመወሰን ደንብ ያወጣል፡፡

፫/ የዚህ ምክር ቤት መቋቋም የሀገሪቷ ሙስሊሞች በክልልም ሆነ በፌዴራል ደረጃ የመሰረቷቸውን በሃይማኖት የተደራጁ ተቋማት መብትም ሆነ ለወደፊቱ የመደራጀትና የመመዝገብ መብታቸውን አይከለክልም፡፡

**፯. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**6. Transitory Provisions**

1/ All properties, obligations and rights obtained before the effective date of this proclamation by all organs of the Ethiopian Islamic Affairs General Council (Mejlis) remain valid.

2/ The General Council may issue Regulation for its internal activity and organization

3/ This Proclamation shall not affect the rights of other religious institutions established by Ethiopian Muslims either at the Federal or Regional level or their right to organize and be registered in the future.

**7. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the *Federal Negarit Gazette.*

**Done at Addis Ababa, on this 4th day of July, 2020.**

**SAHELWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**